ፍኖተ
# ነፃነት
ፍኖተ ነፃነት መጋቢት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል
ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 69



## “አሁን በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ባመዛኙ ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ የባንዳ ልጆች የነበሩ”

አቶ ታዲዎስ ታንቱ
ለኢትዮጵያ ህዝብ ክብር ተቆርቋሪ የግል ተነሳሽነት ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ

7

## በአፋር ክልል ሰዎች በርሃብ እየሞቱ ነው

-ርሀቡ ህዝቡን የከብት ምግብ እንዲበላ አስገድዶታል

4

## የተመስገን ደሳለኝ ብዕር እየዶለዶመ ይሆን?

ዳዊት ሰለሞን

5

## መንግስት ህገወጥ የእስር ዘመቻውን ቀጠለ

### -የአንድነት አባላት ከሰሜን እስከ ደቡብ እየታሰሩ ነው

ኢህአዴግ በሚያዚያ 2005 ዓ.ም ለሚያደርገው የአካባቢና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ምርጫ በአመለካከታቸው የተለዩትን ዜጎች “ለልማትና ለምርጫ እንቅፋት የምትሆኑ ናችሁ” በሚል ፍረጃ በዘመቻ እያሠረ እንደሚገኝ ተገለፀ፡፡ በተለይም የአንድነት ፓርቲ አባላት ላይ ያነጣጠረ ዘመቻ መጀመሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የፓርቲው የሰሜን ቀጠና አደራጅ አቶ አዕምሮ አወቀ ለፍኖተ ነፃነት እንደተናገሩት በቅርቡ የተደረገውን የኢህአዴግ ድርጅቶች ጉባኤ ተከትሎ በአማራ ክልል ባሉ የፓርቲው አባላት ላይ መንግስት ሀይሎች መጠነ ሰፊ ጥቃት እየደረሰባቸው ነው፡፡ አቶ አዕምሮ አክለውም “አባሎቻችንን የማሳደድ የመሰውርና የማሰር ተግባር

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

## የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀመዛሙርት በፌደራል ፖሊስ ከግቢ እናስባርራችኋለን ተብለናል አሉ

10

## ዕውን ኢትዮጵያን የሚመሯት ኢትዮጵያውያን ናቸው?

2

ፍኖተነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡

ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው፡፡ ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው፡፡

## ርእሰ አንቀጽ

# ዕውን ኢትዮጵያን የሚመሯት ኢትዮጵያውያን ናቸው?

የኢትዮጵያ ክብር ተቆርቋሪ የግል ተነሳሽ ኮሚቴና ባለራዕይ ወጣቶች ማህበር ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር በመሆን ያዘጋጁት ሰላማዊ ሰልፍ አላማ ለፋሺስቱና ለጦር ወንጀለኛው ግራዚያኒ በጣሊያን ሀገር የተገነባውን መናፈሻ ስፍራና ሀውልት ለመቃወም ነው፡፡ ይህ ግለሰብ ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈፀመውን ዘግናኝ ጭፍጨፋ ታሪክ አይዘነጋውም፡፡

ግራዚያኒ በመርዝ ጋዝ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ጨፍጭፏል፤ከየካቲት 12 ጀምሮ ለቀናት በዘለቀው የበቀል ጭፍጨፋም በአካፋ ሳይቀር በአዲስ አበባና በአካባቢዋ ያሉ ኢትዮጵያውያንን በግፍ ጨፍጭፏል፡፡ ግራዚያኒ በወቅቱ በሰጠው ትዕዛዝ የፋሺስት ወታደሮች ህይወት ያለውን ተንቀሳቃሽ ፍጥረትን ሁሉ ገድለዋል፡፡ ይህ እሩቅ በማይባል ጊዜ የተፈፀመ ድርጊት ነው፡፡

የኢህአዴግ ባለስልጣናት ለእንዲህ አይነቱ ጨፍጫፊ የተገነባን ሀውልት ለመቃወም በወጡ ዜጎች ላይ የወሰዱት የእስር ተግባር እውን ኢትዮጵያን የሚመሯት ኢትዮጵያውያን ናቸው? አስብሎናል፡፡
ኢህአዴግ በስልጣን ዘመኑ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ በተደጋጋሚ ጥፋት ፈፅሟል፡፡ ሀገራችንን የባህር በር ማሳጣትን ጨምሮ ሀገራዊ ስሜትን አንኳሶ ጠባብ የብሔር ስሜት እንዲንሰራፋ አድርጓል፣ ታሪክን ለስልጣኑ መደላድል ሲል በራሱ መንገድ የሚያዘጋጀው የኢህአዴግ መንግስት ኢትዮጵያን ጠፍጥፎ እንደሰራት ሁሉ ደርግን ለመጣል ካደረገው ትግል ውጪ ያለውን የአርበኞች ተጋድሎ እውቅና ሲሰጥ አይታይም፡፡

መንግስት ለፋሽስቱ ሩዶልፍ ግራዚያኒ የተገነባውን ሀውልት በመቃወም የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ ሳያንስ ግራዚያኒን ለማውገዝ የወጡ ዜጎችን በመደብደብና በማንገላታት ማሰሩ አሳፍሮናል፡፡ ለዜጎቻቸው እና ለሚመሯት ሀገር ክብር የማይሰጡ ይልቁንም የጦር ወንጀለኛና ፋሺስትን ለመቃወም የወጣን ዜጋ ማሰራራቸው የኢህአዴግ ባለስልጣናት ወገንተኝነታቸው ለዜጎቻቸው ነው ወይስ ለፋሺስት? የሚል ዘግናኝ ጥያቄ እንድንሰነዝር ያስገድደናል፡፡

በሰልፉ ላይ የተገኙት ሀገር ወዳድ ዜጎች በማን አለብኝነት ሲታሰሩ ድባደባ ተፈፅሞባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የታሳሪዎቹን የኢሜይልና የማህበራዊ ገፅ የይለፍ ቃል (password) በግዳጅ የሚቀበሉ የደህንነት ሀይሎች ተልከውባቸዋል፡፡ ይህን ቅጥ ያጣ አንባገነናዊ ድርጊት የፈፀመው ወይም እንዲፈፀም ትዕዛዝ የሰጠው አካል ማንነት ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይህባዋል፡፡ በየምክንያቱ ዜጎችን ማሰር የለመደው አንባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት ምን ያክል ኢትዮጵያዊነትን እየተዋጋ እንዳለም የሚያሳይ ድርጊት ነው፡፡ ሰረቱ ዜጎች በማንኛውም ጉዳይ ላይ የተቃውሞም ሆነ የድጋፍ ሰልፍ ማድረግ እንደሚችሉ ህገመንግስቱ ደንግጓል፡፡ ይህን መብት ዜጎች እንዳይጠቀሙ ያፈነው መንግስት፣ ኢህአዴግን የሚደግፉ አልያም በራሱ ከተጠሩ ሰልፎች ውጪ ዜጎች እንዳይሳተፉ በአሰራር ከልክሏል፡፡ ይህ የመብት ረገጣ ከመሆኑም በላይ በዜጎች መካከል 1ኛ ደረጃና 2ኛ ደረጃ ዜግነትን ያስቀመጠ ነው፡፡
የኢህአዴግን ባናውቅም፣ እኛ ኢትዮጵያውያን በቅኝ ገዢዎች የተዋረደ ስነልቦና የለንም፡፡ ሆኖም የግል ጥቅማቸውን ለማደላደል ሲሉ ለቅኝ ገዢ ጠላቶቻችን ያደሩ ባንዳዎች እንደነበሩ ታሪክ በጥቁር መዝገቡ ሸክፎታል፡፡ ይህን አሳፋሪ ተግባር በጣሊያን ወረራ ወቅት የፈፀሙ ኢትዮጵያውያን ለልጅ ልጆቻቸው የሚያስተላልፉት አንገት ቀና የሚያደርግ ታሪክ አይኖርም፡፡
በዚህም ዘመን ተመሳሳይ ክህደት የሚፈፅሙ አካላት መኖራቸው አይጠረጠርም፡፡
የኢህአዴግ መንግስት በይፋ ለጦር ወንጀለኛውና ለፋሺሽቱ ሩዶልፍ ግራዚያኒ የተሰራውን ሀውልት በይፋ ካለማውገዝ ባለፈ ለተቃውሞ የወጡትን ኢትዮጵያውያን በግፍ የማሰሩን ምክንያት ስንመረምር አንድ መራራ እውነት እንረዳለን፤ ይኸውም ጣሊያን ለኢህአዴግ መንግስት ዋንኛዋ ለጋሽ ሀገር መሆኗ ነው፡፡ ይህ የኢህአዴግ መንግስት ተግባር በስልጣን ዘመኑ በኢትዮጵያዊነት ላይ ከፈፀማቸው ክህደቶች እኩል በታሪክ ጥቁር መዝገብ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

# እነ አንዱዓለም አራጌና እስክንድር ነጋ ረቡዕ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ

የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ም/ሊመንበርና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የነበሩት ወጣቱ ፖለቲከኛው አንዱዓለም አራጌና ዓለም አቀፍ ተሸላሚው ታዋቂው ጋዜጠኛና ፓለቲካ ተንታኝ እስክንድርነ ነጋን ጨምሮ ስድስት እስረኞች መጪው ረቡዕ ለውሳኔ 6 ኪሎ የሚገኘው የፌዴራሉ ጠ/ፍ/ቤት ለፍርድ ውሳኔ ይቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡
የአንድነት ፓርቲ ብሔራዊ ም/ቤት አባል ወጣቱ መምህር ናትናኤል መኮንን፣ የመላው ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ/መኢዴፓ/ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ክንፈ ሚካኤል ደበበ፣ የቀድሞ የፓርላማ አባል አቶ አንዱዓም አያሌውና የባህርዳሩ ሻምበል የሺዋስ ይሁንዓለምን ጨምሮ ስድስት ፍርደኞች ረቡዕ የሚቀርቡት ከዚህ ቀደም የከፍተኛው ፍ/ቤት በፈረደባቸው ፍርድ ቅር በመሰኘታቸው ይግባኝ ጠይቀው ነው፡፡ ይግባኙን የተቀበለው ጠ/ፍ/ቤት መሠረትዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት ተፈጥሮአል የተባበትን ጭብጥ ክርክር አድምጧል፣ የዐቃቤ ህግን መልስም ሰምቷል፡፡ በመጨረሻም ክርክሩን ያደመጠው ፍ/ቤት የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት የቀጠረ ቢሆንም በየቀጠሮዎቹ መዝገቡ ተመርምሮ ባመጠናቀቁ በሚል ለ3ኛ ጊዜ መጋቢት 18 ቀን 2005 ዓ/ም ሊቀጥር ችሏአል፡፡ በቀጠሮው መሠረት መጪው ረቡዕ የይግባኙ የፍርድ ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡
አንዱዓለም አራጌና እስክንድር ነጋን ጨምሮ ታሳሪዎቹ የኢህአዴግን መንግስት የሰብአዊና ሌሎች ጥሰቶች ሲተቹ እንደነበር ይታወቃል፡፡

# ፈራሚ ፓርቲዎች በረቂቅ ዕቅድ ላይ ሊመክሩ ነው

ባለፈው ጥቅምት 15 ቀን 2005 ዓ/ም አዳማ ላይ ፔቲሽን ተፈራርመው ስብሰቡን ወደ ትብብር ሠነድ ያሸጋገሩት ፈራሚ ፓርቲዎች ለቀጣይ 6 ወራት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ረቂቅ ዕቅድ ላይ ለመምከር እሁድ ስብሰባ ሊቀመጡ መሆኑን ከጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡
በቅርቡ ፓርቲዎቹ የትብብር ሠነድ ከተፈራረሙ በኋላ ምን እየሠራችሁ ነው በማለት የጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ የሆኑትን አቶ ግርማ በቀለን ጠይቀናቸው ነበር፡፡ አቶ ግርማ በሰጡን መልስ "አራት አብይ ነገሮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ 1ኛ በትብብር ሠነዱ መሠረት ለሚቀጥለው ስድስት ወራት የሚከናወኑ ተግባርና በጀት ረቂቅ እቅድ ማዘጋጀት ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት የቢሮ አደረጃጀት ፣የህዝብ ግንኙነት፣ የማስተዋወቅና ድጋፍ ማሰባሰብን ያካተተ ረቂቅ እቅድ ተዘጋጅቶአል፡፡ 2ኛ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴው እስከአሁን ያከናወናቸውን እቅስቃሴ ሪፖርት ማዘጋጀት ነበር፤ ይህም ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ 3ኛ ጊዚያዊ አስተባባሪ ኮሚቴው የሥራ ሪፖርቱንና ረቅቅ እቅዱን አቅርቦ ኃላፊነቱን ያስረክባል፡፡ በትብብሩ ሰነድ ደንብ መሠረት ፈራሚ ፓርቲዎችን ለሚቀጥለው 6 ወራት የሚመሩትን አስተባባሪ ኮሚቴዎች ማስመረጥ ይሆናል፡፡ 4ኛ በዚሁ መሠረት መጋቢት 15 ቀን 2005 ዓ/ም በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት ስብሰባ እንዲጠራ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡" በማለት መልሰዋል፡፡
በመጨረሻም አቶ ግርማ ሲናገሩ "ከእንግዲህ ከፓርቲዎቹ የሚጠበቀው ጠንካራው ትግላቸውን መግፋት ሲሆን ህዝብ ደግሞ የተነፈገውን ዲሞክራሲያዊ መብትና እየተፈፀመበት ያለውን ሰብአዊ መብት ጥሰት ለማስቆምና ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጎን ቆሞ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፉን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡" ብለዋል፡፡

**በውጭ ሀገር ለምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል ለፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ የህትመት መሳሪያ ማደራጃ ለመግዛት እንዲቻል ጥሪ መቅረቡ ይታወሳል፡፡ በጥሪው መሰረት በርካታ ወገኖቻችን ተግባራዊ ምላሽ እየሰጡ መሆናቸው በወገኖቻችን እንድንኮራ አድርጎናል፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ ወገኖቻችን በገንዘብ አላላኩ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ በመጠየቃቸው ይህን ማብራሪያ አቅርበናል፡፡ ገንዘቡ የሚገባው በቀጥታ በፍኖተ ነጻነት አካውንት ነው፡፡**

1/በኦንላይን እርዳታ ለማድረግ ለምትፈልጉ በፔይፓል (pay pal secure payment)
እነዚህን ድህረ ገጾች ይጎብኙ

http://www.fnotenetsanet.com/
http://www.andinet.org/
http://www.andinetusa.org/

2/ በኤሌክትሮኒክስ ቀጥታ ለምታስተላልፉ

Andinet North America (Finote Netsanet News Paper)
Bank Name : Wells Fargo
ACC# 753-085-0978
Routing # 054-001-220

3/ በቼክ ወይም በገንዝብ ማዘዣ (money order)

Andenet North America (Finote Netsanet News Paper)
P.O.Box 48355
Washington DC 20002
Tel. (202) 462-0556 Fax: (202) 462-0557

ማሳሰቢያ ፡ ገንዘቡን ገቢ ካደረጋችሁ በሁዋላ በሚቀጥለው ኢሜይል አድራሻ ብታሳውቁን ለስራችን ጥራት ይረዳናል፡፡
Email: info@andinetusa.org
ስለትብብራችሁ አስቀድመን ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡
በመላው አለም የምትገኙ ወገኖቻችንም ይህን መረጃ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡

የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ በሰሜን አሜሪካ

# በአፋር ክልል ሰዎች በርሃብ እየሞቱ ነው

## -ርሀቡ ህዝቡን የኩበት ምግብ እንዲበላ አስገድዶታል

በአፋር ክልል ዞን አንድ ኤሊዳኣልና ቢሩ በሚባሉ ወረዳዎች ከፍተኛ የሆነ ርሃብ መከሰቱን የፍኖተ ነፃነት ምንጮች አስታወቁ፡፡

እንደምንጮቹ መረጃ በተለይ በሁለቱ ወረዳዎች የረሃቡ ሁኔታ እጅግ ከመክፋቱ የተነሳ በአካባቢው ምግብና ውሃ በመጥፋቱ ከፍተኛ ርሃብ ተከስቷል፡፡ ከርሃቡ አስከፊነትም የተነሳ ለከብቶች መኖ "አብዳ" የሚባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት የሰጠውን ፉርሽካ ነዋሪዎች ጋግረው መብላት መጀመራቸውን የፍኖተ ነፃነት ምንጮች ከስፍራው ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በስፍራው ባለ25 ሊትር ውሃ እስከ 200 ብር እየተሸጠ ከመሆኑም በተጨማሪ በተከሰተው ርሃብ እስካሁን 7 ሰዎች መሞታቸውንም ምንጮቻችን ከስፍራው የዓይን እማኞችን ጠቅሰው ዘግበዋል፡፡

የክልሉ መንግስት ባልታወቀ ምክንያት እስካሁን ምንም ዓይነት የዕርዳታ ድጋፍ ባለማድረጉ ያካባቢው ነዋሪዎች ቅሬታ ቢያቀርቡም እስካሁን ምላሽ አለመስጠቱ ተነግሯል፡፡ በግብርና ሚ/ር አደጋ መካላከል ዝግጁነት አስተባባሪ መስሪያ ቤትም እስካሁን ምላሽ አለመስጠቱ ተጠቁሟል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም በተጠቀሱ ወረዳዎች የተከሰተው ርሃብ ያደረሰውን ጉዳትና መንግስት እየወሰደ ያለውን እርምጃ ጠይቀን የአፋር ክልል የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ አቶ መሐመድ "የደረሰውን ጉዳት ገና እያጣራን ነው፣ ልዑካንን ወደ አካባቢው ልከናል፤ አደጋ መከላከል መረጃውን ስላልሰጠን ባልተጣራ ጉዳይ ላይ መረጃ ልሰጥ አልችልም " ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

# የአንድነት ብሄራዊ ምክር ቤት ትላንት ስኬታማ ስብሰባ አካሄደ





በትላንትናው እለት የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርተ ብሄራዊ ምክር ቤት ስኬታማ ስብሰባ እንዳደረገ የምክርቤቱ አፈጉባኤ ገለፁ፡፡

የምክር ቤቱ አፈጉባኤ አቶ ዘካሪያስ የማነብርሃን ለፍኖተ ነፃነት እንደገለፁት ምክር ቤቱ በትላንትናው ዕለት በስድስት አጀንዳዎች ላይ ውይይት አድርጎ ውሳኔዎችን አስተላልፏል፡፡ ምክር ቤቱ በአንድነት የአምስት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት በዚህ አመት መጨረሻ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ወስኖ ጉባኤውን የሚያመቻች ሰባት አባላትን ያካተተ ኮሚቴ መርጧል፡፡ ፓርቲው በ2005 በሚያደርገው ጠቅላላ ጉባኤ አዳዲስ አመራሮች ሊመረጡ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡
የአንድነት ብሔራዊ ምክር ቤት 45 ቋሚ አባላት 15 ተለዋጭ አባላትና 5 የኢዲትና ኢንስፔክሽን አባላትን ያካተተነው፡፡

# የተመስገን ደሳለኝ ብዕር እየዶለዶመ ይሆን?

በዳዊት ሰለሞን

ከሳምንት በፊት ተመስገን ደሳለኝን ሲያዳልጠው የምትል ጽሁፍ አስነብቤ ነበር፡፡ የጽሁፉ አጠቃላይ ምልከታ ተመስገን በልዕልና ጋዜጣ ‹‹የተቃዋሚዎች ድክመትና ለስልጣኑ ያላቸው ርቀት››በማለት ላቀረበው ሰፋ ያለ ጽሁፍ በተለይም አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን በተመለከተ ለሰነዘራቸው አንድ ጫፍ ለረገጡ አስተያየቶች በበኩሌ የማውቃቸው እውነታዎች በተመስገን እንደተባለው አለመሆኑን ለማሳየት ነበር፡፡

ከሳምንት በኂላ ደግሞ ለንባብ የበቃችው ልዕልና ጋዜጣ እኔ በፌስ ቡክ የለቀቅኩትን ጽሁፍ የፓርቲው ማስተባበያ በማደረግ ‹‹አንድነት ፓርቲ ብሄራዊ ቡድኑን አስመልክቶ የወጣውን መግለጫ አስተባበለ፡፡›› በማለት ለንባብ አብቅቶታል፡፡

እኔ በራሴ ስምና የግሌ አስተያየት መሆኑን ደጋግሜ የገለጽኩበት ጽሁፍ እንዴት ተደርጎ የአንድነት ማስተባበያ ተደርጎ ሊገለጽ እንደሚችል የሚያውቁት ከመነሻው ፓርቲውን ለመተቸት ብዕራቸውን ከወረቀት ያገናኙ ብቻ ናቸው፡፡ “የተቃዋሚዎች ውስጣዊና ውጫዊ ችግር ተፈትቶ ለስልጣን የሚበቁበት ዘመን እንዲመጣ እመኛለሁ” በማለት እንደ አንድ ጋዜጠኛ ሳይሆን እንደ ስትራቴጂስት ስልት ሲቀይስና ሲመክር የነበረ ግለሰብ እንዴት ፓርቲው ያልሰጠውን ማስተባበያ ፓርቲው እንደሰጠ በማድረግ አንባቢን ውሸት ይመግባል? በዚህስ በውሸት ከምንከሳቸው የገዢው ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ማሰራጫዎች በምን እንለያለን?

የልዕልና ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጽሁፌን የፓርቲው ማስተባበያ አድርጎ የወሰደው በፍኖተ ነፃነት ኒውስ ሌተርና ኦን ላይን ሚዲያ አማካኝነት እንዲሰራጭ በመደረጉ ሊሆን ይችላል፡፡ ለማንኛውም ይህም ቢሆን ፓርቲው ማስተባበያ እንደሰጠ ተደርጎ ለመውሰድ የሚያስደፍር አይደለም፡፡ ምክንያቶቼን ልዘርዝር

1)ጽሁፌ የሚጀምረው ለተመስገን ያለኝን አድናቆት በመግለጽ ነበር፡፡ ለእርሱ ያለኝን ወዳጃዊ ስሜት ለማንጸባረቅም በቁልምጫ ‹‹ተሜ›› በማለት ስሙን አንስቼያለሁ፡፡ እንዴት ነው ወዳጆቼ ፓርቲ ማስተባበያ በቁልምጫ እየጠራ ሲያወጣ አልታያችሁም?

2)ፓርቲው ለጽሁፉ ምላሽ እንዲሰጥ በመሻት ከአመራሮቹ ለአንዱ በመደወል ጆሮዬን ጭው ያደረገ ምላሽ እንደሰጠኝ ገልጬ ነበር፡፡ እንዴት ነው የፓርቲው ጆሮ ጭው የሚለው?

3)በጽሁፌ ደጋግሜ ፓርቲው እያልኩኝ ጠቅሻለሁ፡፡ ማስተባበያው በፓርቲው እውቅና የወጣ ቢሆን ኖሮ ‹‹ፓርቲያችን››በሚሉ ቃላቶች የሚደገፍ ይሆን ነበር፡፡ አይመስላችሁም ?

4)የጽሁፌ ማሳረጊያ ‹‹በግሌ ተሜ የመግለጫውን ሙሉ ቃል ሳያነብ ለትችት መቻኮሉ አግራሞት ጭሮብኛል›› የሚል አረፍተ ነገርን ሰርቷል፡፡ በግሌ ማለት ምን ማለት ይሆን? እረ የጋዜጠኝነት ኤቲክሱን ምን በላው ?

5)በአንድነት ልሳን ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ላይ ስሰራ እንደ መቆየቴ በፍኖተ ነጻነትና በፓርቲው መካከል ያለውን ቁርኝት እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡ ፓርቲው ጋዜጣው በፓርቲው አመለካከት ብቻ እንዳይታጠርና የሌሎች ሀሳብ እንዳይታፈን በማሰብ ፍኖተ ነጻነት የሁሉም ልሳን እንድትሆን በወሰደው ውሳኔ መሰረት ኢህአዴጋውያን ሳይቀሩ ሀሳብን በሀሳብ ለመሞገት ቢነሱ በሩን ክፍት በማድረግ የማገልገል የሞራል ዝግጁነት ነበረው፡፡ ፍጹም የስራ ነጻነት የነበራቸው የጋዜጣው አዘጋጆች(ዋና አዘጋጁ ነብዩ ሀይሉ የፓርቲው አባል አልነበረም) ሞያው ለሚጠይቀው ዲሲፕሊን በመገዛት መንፈስ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ገዢው ፓርቲን የተቹ የባልደረቦቼ ብዕሮች በተቃዋሚው ጎራ (አንድነትን) ጨምሮ ለተመለከቷቸው ስህተቶች አልራሩም፡፡ ይህም ጋዜጣይቱን ከፓርቲ ልሳንነት ባሻገር የሁሉም አድርጓት በሳምንት ሁለት ጊዜ እስከ መታተም በመድረስ የአንባቢዎቿን ቁጥር 20,000 አድርሳ ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ የእኛ ጋዜጣ በመሆኗ እኛ ብቻ ልንናገርባት ይገባል ያላሉትን የፓርቲውን አመራሮችና አባለት ላመስግን፡፡ እናንተ ለስልጣን ብትበቁ ኢቴቪ ምን አይነት መልክ ሊኖረው እንደሚችል በፍኖተ ነጻነት አሳይታችሁኛልና ምስጋና ይሁንላችሁ፡፡

6)ከጽሁፉ ስር ዳዊት ሰለሞን የሚለው ስሜ መስፈሩ ምን ያመለክታል? ይህ ጥያቄ ነጩን ነጭ የማለት ድፍረት ለሌለው ብዕር መጠየቅ ከባድ ሊሆን ይችላል፤ ግን አንድነት እንዴት ዳዊት ይሆናል? ልዕልና የእኔን ጽሁፍ የፓርቲው በማድረግ ካወጣች በኂላ አንድ ወዳጄ ደውሎ እንደምን ዋሉ ክቡር ሊቀመንበር ብሎኛል፡፡ እንዴት ነው ዶ/ር ነጋሶ ላይ መፈንቅለ ስልጣን አደረግኩ እንዴ ?

## አስቂኙ የማስተባበያ ማስተባበያ

“አንድነት ማስተባበያ አወጣ” በማለት ዜና የሰራችው ልዕልና ጋዜጣ ሳትነግረን ለማስተባበያው የራሷን ማስተባበያ አውጥታለች፡፡ አንድነት የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን አከበረ ያለው የተመስገን ጽሁፍ የመረጃ ምክነት እንዳለበት መጥቀሴ አይዘነጋም፡፡ አሁን ልዕልና ያኔ ተሜ ያልጠቀሰውን መረጃ በማውጣት ፓርቲው በ2003 ቀኑን ማክበሩን ፍትህ ጋዜጣ ዘግባ ነበር ብላናለች፡፡ አስቂኙ ነገር ፍትህ ዘግባ ነበር መባሉ ነው፤ በቃ ፍትህ የዘገበችው ሁሉ እውነት ነው ማለት ነው? ወይ ልዕልና! አሁንም ማስረጃው ስስ ነው፡፡ አንድነት የባህል ቀንን እንጂ የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን በኢህአዴግ ቀረርቶ አክብሮ አያውቅም፡፡ ለአንድነት የብሄር ብሄረሰቦች ጉዳይ በዕለቱ ከመጨፈር ብዙ ይርቃል፡፡ ገዢው ፓርቲ የብሄር ጉዳይን የያዘበት መንገድ ለኢትዮጵያ የማይበጅ መሆኑን በማመኑን አጥብቆ ይታገለዋል፡፡ ልዕልና ሆይ ይህን ማወቅ ከፈለግሽ የፓርቲውን ፕሮግራም ለማንበብ ሞክሪ፡፡

ስለ ብሄራዊ ቡድኑ የጠቀስኩት ነገርም ቅንነት በጎደለው መልኩ ተንሸዋርሮ ቀርቧል፡፡ “አንድነት መግለጫውን ማውጣቱን አስተባበለ” በማለት ልዕልና አቧራ ለማስነሳት የሞከረች ቢሆንም በወቅቱ እኔ ያልኩት ተመስገን የመግለጫውን መንፈስ አልተገነዘበውም፡፡የመልእክቱን አንኳር ነጥብ ስቶታል እንጂ መግለጫው አልወጣም አላልኩም፡፡ በአንድ ቋንቋ እየጻፍን ይህን ያህል የባቢሎን ግንብ ሰራተኞች የመሰልንበት መንገድ ምስጢር ሆኖብኛል፡፡ እናም ነገሬን ልስፈር የሳምንቱም ጽሁፍ ሆነ የአሁኑ የእኔ (የዳዊት) እንጂ የፓርቲው አይደለም፡፡ ሳላውቀው የሳምንቱን ጽሁፍ በአንድነት ማህተም አውጥቼው ከነበረም ይነገረኝና ሂሴን ላዋጥ፡፡

## ከዋና አዘጋጁ

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ልሳን ነች፤ ከጋዜጣዋ ምስረታ አንስቶ በሀገራችን ያለውን የነፃ ፕሬስ አፈና በመገንዘብ ፓርቲው የሌሎች ፓርቲዎችም ሀሳብ እንዲተላለፍበት ልሳኑን የህዝብም እንድትሆን አድርጓል፡፡ አንድነት ለነፃ ፕሬስ ማበብ የከፈለውንም ውለታ ታሪክ የሚያነሳው ይሆናል፡፡

የፍኖተ ነፃነት አንባቢዎች እንደሚያስታውሱት “…ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው፡፡ ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለመግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው፡፡” የሚል መልዕክት በርዕሰ አንቀፁ ራስጌ ይሰፍር ነበር፡፡ ይሄው (እንደነፃ ፕሬስ የማገልገል አላማ) የጋዜጣዋ መሰረት በመሆኑ በአሳታሚው በአንድነት ፓርቲና በአመራሮቹም ላይ ያነጣጠሩ ትችቶች በፍኖተ ነፃነት ላይ እንዲስተናገዱ በርከፍቷል፤ሆኖም ፓርቲውም ሆነ አመራሮቹ እንዴት በገዛ ልሳናችን እንተቻለን የሚል ስሞታ አላቀረቡም፡፡ የጋዜጣችን ለሁሉም ወገን ነፃ አስተያየቶች ክፍት መሆን በመገንዘብ የኦህዴድ/ኢህአዴግ ባለስልጣናትም የላኩልንን ጽሁፍ ማውጣታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡
የአንድነት ፓርቲ ኤዲቶሪያል ፖሊሲም በፍኖተ ነፃነትም ሆነ ወደ ፊት ስራቸውን በሚጀምሩት የፓርቲው ብዙሀን መገናኛዎች ነፃ ሀሳቦች እንደልብ እንዲንሸራሸሩና ጋዜጠኞችም ከየትኛውም (የውስጥም ሆነ የውጪ) ጫልቃ ገብነት ነፃ ሆነው ሙያዊ

# “አሁን በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ባመዛኙ ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ የባንዳ ልጆች የነበሩ”

## አቶ ታዲዎስ ታንቱ
## ለኢትዮጵያ ህዝብ ክብር ተቆርቋሪ የግል ተነሳሽነት ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ



የዛሬው እንግዳችን አቶ ታዲዎስ ታንቱ ይባላሉ፡፡ አቶ ታዲዎስ የታሪክ ምሁርና በኢትዮጵያ ፖለቲካ እና ነፃ ፕሬስ ውስጥ ትልቅ ሚና ያላቸው ሲሆን በአሁን ወቅት “ለኢትዮጵያ ህዝብ ክብር ተቆርቋሪ የግል ተነሳሽነት ኮሚቴ” ዋና ሰብሳቢ ናቸው ፡፡ በተለይ ለፋሺስቱ ግራዚያኒ ከተሰራው ሐውልት ጋር በተያያዘ አጭር ቆይታ አድርገናል ተከታተሉን፡፡

**በጣሊያን የሩዶልፍ ግራዚያኒን የሐውልት ለመቃወም የሐሳቡ ጠንሳሽ ማን ነው?**

አቶ ታዲዎስ፡- የፋሽቱ ጣሊያን የኢትዮጵያውያን ዋና ጨፍጫፊ የነበረውን ሩዶልፍ ግራዚያኒ ሐውልት መስራት ለመጀመሪያ ጊዜ ተቃውሞው የተጀመረው በውጭ ሀገር ባሉ ኢትዮጵያውያን ነው፡፡ በሀገር ውስጥ ግን የሐሳቡ ጠንሳሽ “ለኢትዮጵያ ህዝብ ክብር ተቆርቋሪ የግል ተነሳሽነት ኮሚቴ” ነው፡፡ ከዛ በኋላ የባለዕራዕይ ወጣቶች ማኅበር ሰልፉን ለማስተባበር ፈቃደኛ መሆኑን ገለፀልን፤ በዚህም ላይ ሰማያዊ ፓርቲ እንደሚተባበረን ከገለፀ በኋላ መጋቢት 8 ቀን 2005 ዓ.ም. ሰልፉን ለማካሄድ ወሰንን፡፡

**ተቃወቅሞውን ለማቅረብ ያነሳሳችሁ ዋነኛ ምክንያት ምን ነበር?**

ብዙውን ጊዜ እኔ በጋዜጦች ስለ አርበኞች ታሪክ ያነበብኩትንና ያወቅሁትን እፅፋለሁ፣ እመረምራለሁ፡፡ የጣሊያኑ ፋሽስት ግራዚያኒ ሀገራችንን በመውረር በአባቶቻችንና እናቶቻችን አርበኞች ላይ የፈፀሙት የግፍ ግድያ አሰቃቂ እንደነበር ስለተረዳሁ፤ ያ ሲቆጨኝ ደግሞ አሁን በጣሊያን ሀገር ለእሱ ሙዚየምና ሐውልት የመሰራቱን ወሬ ከኢንተርኔት ምንጮች ስላየሁ በጣም ተናድጄ እንደውም ተቃውሞ ማሰማት አለብን ብዬ ተነሳሁ፡፡ በኋላ ደግሞ እኛም የአንተ ዓይነት ሐሳብ ነበረን ብለው የባለ ዕራዕይ ወጣቶች ማኅበር አነጋገሩን፡፡ ከዛ በመቀጠል ሰማያዊ ፓርቲ በጋራ እንስራ የሚል ጥያቄ አቀረበ፡፡ በዚህ ምክንያት ሶስቱ አካላት በጋራ ሰልፉን ለማድረግ ዝግጅት ማድረግ ጀመርን፡፡ ስለዚህ ለኢትዮጵያ ጠላት አይደለም ጣሊያን ሀገር ጨረቃም ላይ ቢሆን ሀውልት እንዲሰራ አንፈቅደም፡፡

በጊዜው ሩዶልፍ ግራዚያኒ ወንጀለኛ በመሆኑ የነበረው ፊልድ ማርሻል ማዕረግ ተገፎ ከወታደርነቱ ተባሮ በጦር ወንጀል ተከሶ 19 ዓመት ተፈርዶበት ቅጣቱን ሳይጨርስ ከእስር ቢለቀቅም እ.አ.አ. በ1955 ዓ.ም. ሞቷል፡፡ ታዲያ ይህ በጊዜው ወንጀለኛ ለተባለው ሰው ሐውልትም ሆነ የመታሰቢያ ሙዚየም ማሰራት ኢትዮጵየውያንን መናቅና የአባቶቻችንን ክብር የሚነካ በመሆኑ ሊሰራለት አይገባም፤ እንደውም ለፈፀመው እልቂት ጣሊያን በቂ ካሳ ስላልከፈለች ካሳ መክፈልና በይፋ ይቅርታ መጠየቅ ይገባታል የሚል አቋም ይዘን ነው የወጣነው፡፡ ስለዚህ ግራዚያኒ ከነ አዳፋ ታሪኩ ሌላው እንዳይደግም ሲወሳ መኖር አለበት እንጂ እንደ ጀግና ሐውልት ሊሰራለት፣ሊወደስና ሊመሰገን አይገባም እንላለን፡፡

**በወቅቱ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ይቻላል?**

በወቅቱ ግራዚያኒ በፊርማው በግፍ ኢትዮጵያውያንን ያስጨፈጨፋቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ከነደብዳቤው አለ፤ የዚህ ቅጂ እኔም ጋር አለ ይታወቃል፡፡ በተለይ የካቲት 12-14 ቀን 1929 ዓ.ም. ከ30 ሺህ በላይ ዜጎቻችንን በግፍ አዲስ አበባ ላይ እራሱ ግራዚያኒ አስጨፍጨፏል፡፡ ከ250 በላይ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስን ጨምሮ መነኮሳትን አስጨፍጭፏል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግስት በ1938 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በፈረንሳይ ፓሪስ በተካሄደው አለም አቀፍ ጉባኤ ያቀረበው ሰነድ እንደሚያስረዳው 760,300 ሺህ ዜጎች ወዲያው ሲገደሉ 525,000 ደግሞ ከነቤት ንብረታቸው እንዲቃጠሉ ተደርጎ ህይወታቸው አልፏል፡፡ ከሁለት ሺህ በላይ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለው መነኮሳት ተገድለዋል፣ በርካታ ቅርሶች ተዘርፈው ተወስደዋል፡፡ በርግጥ ከተዘረፉ ቅርሶቻችን መካከል እስካሁን የተመለሰው የአክሱም ሐውልት ብቻ ነው፤ ሌሎቹ ግን አሁንም እዛው ናቸው፤ ሊመለሱልንም ይገባል፡፡ ከዛ ውጭ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የቀንድ ከብቶች በወቅቱ ተዘርፈው ተወስደዋል፤ 7 ሺህ ግመሎችም ተገድለውብናል፡፡ ይህም በሰነድ በተደገፈ ማስረጃ ለዓለም አቀፉ የሰላም ጉባዔ የቀረበ ነው፡፡ በወቅቱ ሰነድ ያልቀረበባቸውና ሰፊ ጥናቶች ሊደረግባቸው የሚገቡ በርካታ ጥፋቶች

▶

ተፈፅመዋል፡፡

**ይህንን ተቃውሞ በዋነኝነት ማቅረብ የነበረበት መንግስት ነበር የሚሉ ወገኖች አሉ፤ እርስዎስ ምን ይላሉ?**

እኔም እስማማለሁ፤ ነገር ግን መንግስት ማዘጋጀት ካልቻለ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ማዘጋጀት ይችላል፡፡ እኔ እንደሚገባኝ መንግስት ተቃውሞ ያላቀረበው ከጣሊያን የሚያገኘው ዕርዳታ ይቀርብኛል በሚል ይመስለኛል፡፡ እኔ እስከማውቀው ይሄ መንግስት ዕለታዊና የፖለቲካ ገበያ ጥቅምን መሰረት ያደረገ እንጂ ወደፊት ትውልድ የሚኮራበትን ስራ የመስራት ዓላማ የለውም
፡፡ ከዚህ በፊት የቀደሙ አባቶቻችን የሰሩትን በጎ ታሪኮች ሲያንቋሽሽ የኖረ መንግስት ስለሆነ እንዲህ ዓይነት የአባቶቻችንና እናቶቻችን አርበኞች ታሪክና ክብር የሚያስጠብቅ ስራ ይሰራል ብዬ አላስብም፡፡
ነገር ግን ኢትዮጵያዊ ስሜት ያለው፣ ብሔራዊ ስሜትን የጠበቀ ህዝባዊ መንግስት ቢሆን ኖሮ ህዝቡን አስተባብሮ ይሄንን ስራ በቀዳሚነት መስራት የነበረበት እሱ ነበር፡፡ ስለዚህ መንግስት ባያደርግም ዜጎች ይህንን ሰልፍ የማድረግ መብት ስላላቸው እኛም ሰልፉን አድርገናል፡፡

**የኢትዮጵያ መንግስት የሀውልት ግንባታውን አለመቃወሙ ምን ያስረዳናል?**

ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በእጅ አዙር ለሀውልት ግንባታው እውቅና እንደሰጠ ይቆጠራል፤ ይህንን እኔም አምናለሁ፡፡ ከዚህም በላይ አሁን በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ባመዛኙ ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ የባንዳ ልጆች የነበሩ ናቸው፡፡
እንደውም ነፃነታችንን ባወጅንበት ሁለት ዓመት ሳይሞላ በአርበኞች ላይ ጦርነት የከፈቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ለግራዚያኒ የጀግና ሐውልት መሰራቱን ባይቃወሙ አይገርመኝም፤ ምክንያቱም እነሱ የማን ልጆች ናቸው? እስኪ በስልጣን ላይ ካሉት (ከኢህአዴግ) መካከል ለሀገሩ እና ለወገኑ ብሔራዊ ስሜት፣ ነፃነትና ክብር የተዋጋ የአርበኛ ልጅ አንድ ሰው ካለ ንገረኝ? አንድም ሰው የለም፡፡ ስለዚህ የባንዳ ልጅ ለጨፍጫፊው ግራዚያኒ በእጅ አዙርም ሆነ በቀጥታ እውቅና በመስጠት ድጋፍ ቢያደርጉ አያስደንቀኝም፡፡

**እናንተ ሰላማዊ ሰልፉን ከማድረጋችሁ አንድ ቀን በፊት መጋቢት 7 ቀን 2005 ዓ.ም ስምንት ሰዎች መታሰራቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ክስተት በሰልፉ ወቅት እስር እንደሚኖር አልጠቆማችሁም?**

እሱን አውቀንም ነው ሰልፍ የወጣነው፡፡ አንድ ቀን አስቀድሞ ሌሎች ቢታሰሩም መውጣት አለብን ብለን ነው የወጣነው፤ እኛም ብንታሰር ሌሎችም እንደሚወጡ እናውቃለን፡፡ ችግር ይፈጠራል ብለን አልተውንም ፤መተውም የለብንም፡፡ ምክንያቱም ይሄ የሀገርና የወገን ጉዳይ ነውና፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሰልፉ ላይ የተገኙትን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

> **የኢትዮጵያ መንግስት በ1938 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በፈረንሳይ ፓሪስ በተካሄደው አለም አቀፍ ጉባኤ ያቀረበው ሰነድ እንደሚያስረዳው 760,300 ሺህ ዜጎች ወዲያው ሲገደሉ 525,000 ደግሞ ከነቤት ንብረታቸው እንዲቃጠሉ ተደርጎ ህይወታቸው አልፏል፡፡ ከሁለት ሺህ በላይ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለው መነኮሳት ተገድለዋል፤ በርካታ ቅርሶች ተዘርፈው ተወስደዋል፡፡**

**የታሰራችሁት ምን ወንጀል ሰርታችኋል ተብላችሁ ነው?**

ፍቃድ አልጠየቃችሁም ፣ አላስፈቀዳችሁም በሚል ነው፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ በነበሩ የአጼ ኃይለስላሴ፣ በደርግ ዘመንም ሆነ አሁንም በወያኔ አገዛዝ ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት ፈቃድ ይጠየቃል የሚል የተፃፈ ህገመንግስትም ሆነ አዋጅ አልነበረም፤የለምም፡፡ ዋናው ከእኛ የሚጠበቀው ሰላማዊ ሰልፍ እንደምናደርግ ማሳወቅና አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግ ማድረግ እንጂ ፈቃድ መጠየቅ አይደለም፡፡ ይህንንም ለእኛ ጥቅም እንጂ እነሱን ለማስደሰት አይደልም፡፡ እኛ ደግሞ የሀገሪቱን የተፃፈ ህግ ተከትለን ሰልፉን ከማድረጋችን 10 ቀናት አስቀድመን አሳውቀናል፡፡

**ኢትዮጵያውያንን በግፍ ለጨፈጨፈው ግራዚያኒ የተሰራለትን ሐውልት በመቃወማችሁ በኢትዮጵያ መንግስት መታሰራችሁ ምን ስሜት ፈጠረባችሁ?**

ለእኛ የበለጠ የተነሳሽነት ስሜት ሰጥቶናል፡፡ ጉዳዩንም አጠናክረን እንድንሄድ ትልቅ የሞራል ድጋፍ ሆኖናል፡፡

**ከእስር ሲለቋችሁ ምን ብለው ነው?**

ምንም ሳይሉን ለሁለት ሰው አንዳንድ ዋስ በማስጠራት ለቀውናል፡፡ ምክንያቱን ግን አልነገሩንም፤አላወቅንም፡፡ ከዛ ስትፈለጉ ትመጣላችሁ ብለው በዋስ ለቀውናል፡፡

**በታሰራችሁበት ወቅትስ የገጠማችሁ ችግር አለ?**

በርግጥ እኔ ላይ ድብደባ አልፈፀሙም እንጂ ተመትተው ፊታቸው በተለይም አፋቸው አካባቢ የደማ ወጣት አይቻለሁ፡፡ ፊታቸው ያባበጠ ወጣቶችንም አይቻለሁ፡፡ ሌሎችንም ወጣቶች እንደደበደቧቸውም ሰምቻለሁ፡፡ በተለይ ደህንነቶች ማታ መጥተው በግል እያስጠሩ በቢሮ ያናግሩ ነበር፡፡ ስራው ግን የፖሊሶች እንጂ የደህንነቶች አልነበረም፡፡
በታሰርንበት ዕለት ያለምግብና ውሃ ቀን ሙሉ እንድንውል ተደርገናል፡፡ በተለይ እስር ቤቱን ስቃይ አራዳ ፖሊስ መምሪያና ጃንሜዳ ፖሊስ ጣቢያ ያለውን ስታይ ዕቃ ለማስቀመጥ ሆነ ለሌሎች እንስሳቶች ለአንዲት ደቂቃ እንኳን እንዲቆዩበት አይመችም፡፡ እስር ቤቱን ስታይ በጣም ያሳዝናል፤ እዛ የገቡ እኮ ጤነኛ ሆነው የመውጣታቸው ዕድል እራሱ አነስተኛ ነው፤ለበሽታ የሚያጋልጡ ብዙ ነገሮች አሉ፤ ብቻ በጣም ያሳዝናል፡፡
ይሄ ደግሞ የወንበዴ ስራ ነው፤ ይሄንን መንግስት ማረም አለበት፡፡ ሌላው መርማሪ ፖሊሶችና ደህንነቶች ያልተገቡና ከእስሩ ጋር የማይገናኙ የግል ህይወትን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፣ የኢ-ሜይል የይለፍ ቃል ይጠይቃሉ፣... ብቻ ብዙ ነው፡፡ በግል እኔን ደግሞ ፊታቸውን በኮፊያ የሸፈኑና ጥቁር መነፅር ያደረጉ ደህንነቶች ዋስ ጠርቼ ከወጣሁ በኋላ አንተ የአርበኞችን ታሪክ እያነሳሳህ ወጣቶችን እያነሳሳህ ስለሆነ ብታርፍ ይሻልሃል፤ በግል ልናናግርህ እንፈልጋለን እያሉ ለማስፈራራት ሞክረዋል፡፡ እኔ ግን በህጋዊ ደብዳቤ ያውም ያመንኩበት ካልሆነ ብትጠሩኝ አልመጣም፤ አላናግርም ብያለሁ፡፡

**ከዚህ በኋላስ ይህን ተቃውሞ ለመቀጠልስ እቅዱ አላችሁ?**

አዎ አለን፡፡ ይህ ተቃውሞ ምላሽ አግኝቶ ያሰብነው እስኪሳካ እንቀጥላለን፡፡ ነገር ግን ዝርዝር ሁኔታውን በተመለከተ እያጠናን ስለሆነ ወደፊት ሀገር ውስጥ ያለነው ውጭ ካሉ ወገኖቻችን ጋር በመመካከር ምን መልክ መያዝ እንዳለበት ስንወስን ይፋ እናደርጋለን፡፡

**በመጨረሻም የሚሉት ነገር ካለ ዕድሉን ልስጥዎት**

ህዝቡ ዓላማችን ከግብ እንዲደርስ የተለመደ ድጋፉን ከመስጠት ወደ ኋላ እንዳይል አደራ እላለሁ፡፡

# በኢትዮጵያ የፍትህ መጓደሉ ተባብሶ ቀጥሏል

## -ባንቢስ ላይ የተመሰረተው ክስ በመንግስት ትዕዛዝ ተቋረጠ

መንግስት በህዝብ ደህንነት ላይ ችግር የፈጠሩ ግለሰቦችን ለኢህአዴግ ስለጠቀሙ ብቻ ከተከሰሱበት ወንጀል ነፃ እንዲሆኑ እያደረገ ነው ሲሉ ምንጮቻችን ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል፡፡

ነገር ግን የኢህአዴግ ስጋት ናቸው የሚባሉ ንፁሃንን በግፍ አሸባሪ እያሉ እያሰሩና እሰቃዩ ባሉበት ሰዓት ለህዝብ ስጋት የሆኑት ግን ለኢህአዴግ ስለጠቀሙ ብቻ ምንም ወንጀል ቢሰሩ በነፃ ይለቀቃሉ ሲሉ የፍትህ ስርዓቱን የሚከታተሉ የህግ ባለሙያዎች አስታወቁ፡፡ በዚህም ምክንያት ዜጎች በሀገራቸው ኢህአዴግ በሚፈጥረው የተዛባ የፍትህ ስርዓት ምክንያት በሰላምና በጤና የመኖር ዋስትናቸው አደጋ ላይ መውደቁን እነዚሁ የህግ ባለሙያዎች አስታውቀዋል፡፡

ባለሙያዎቹ እንደማሳያ የሚጠቅሱት ባምቢስ ሱፐር ማርኬት በርካታ የተበከሉና ጊዜ ያለፈባቸውን የታሸጉ ምግቦች ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሲሸጥ እጅ ከፍንጅ ተይዞ ከነሐሴ 23 እስከ ጳጉሜ 4 ቀን 2003 ዓ.ም. 22 ማዞሪያ በሚገኘው የካራማራ ፖሊስ ጣቢያ በአንድ አይሱዙ ሙሉ ጭነት ወስዶ ማቃጠሉ ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ ድርጅቱና የሱፐር ማርኬቱ ባለቤት ግሪካዊው ባለሃብት ሚስተር ባምቢስ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት ተከሰው ሐምሌ 2004 ዓ.ም. ሊሰጥ የነበረው ክስ የፍርድ ውሳኔ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡

ክሱ ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት ለማጣራት በፍትህ ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ወደ ሆኑት አቶ ደሳለኝ ታረቀኝ ምላሽ እንዲሰጡን ከአንድ ሳምንት በላይ ጥረት ብናደርግም “አጣርቼ እነግራችኋለው” ካሉ በኋላ መልስ ሊሰጡን አልፈለጉም፤ በመጨረሻ ስብሰባ ላይ ነኝ በማለት ምላሻቸውን ሊሰጡን አልቻሉም፡፡

# ናትናኤል መኮንን ቤተሰብ እንዳይጎበኘው ተከለከለ



የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል የሆኑትና በቃሊቲ ቂሊንጦ ልዩ ከፍተኛ ጥበቃ የሚደረግበት ወህኒ ቤት በእስር ላይ የሚገኙት አቶ ናትናኤል መኮንን ከሐሙስ መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ ምክንያቱ ባልተገለፀበት ሁኔታ ከወዳጅ ቤተሰብ እንዳይገናኝ መከልከሉ ተረጋገጠ ፡፡

ይህንንም የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ባልደረባ ከባለቤቱ ወይዘሮ ፍቅርተ ጋር በመሆን ቅዳሜ መጋቢት 14 ቀን 2005 ዓ.ም እዛው ቃሊቲ ቂሊንጦ ወህኒ ቤት በአካል በመሄድ ማረጋገጥ ችሏል፡፡

አቶ ናትኤል መኮንን በምን የህግ አግባብ ለአንድ ወር ከወዳጅ ቤተሰቦቹ በተለይም ዘወትር ከሚጠይቁትና ስንቅ ከሚያመላልሱለት ባለቤቱና ልጁ እንዳይገናኝእንደተደረገየፍትህሚኒስቴር የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ የሆኑትን አቶ ደሳለኝ ታረቀኝን የጠየቅናቸው ሲሆን እሳቸውም “ታራሚዎች ከቤተሰቦቻቸው እንዳይገናኙ የሚያዝ ህግ የለም በይበልጥ የማረሚያ ቤቱን ኃላፊ ኮማንደር አስቻለው መኮንን መልስ ይስጧችሁ” በማለት መርተውናል፡፡

ኮማንደር አስቻለው በበኩላቸው “በርግጥ እስረኛ የማረሚያ ቤቱን ስነምግባር ከጣሰ በማረሚያ ቤቱ አሰራር መሰረት ቅጣት ይኖራል፤ ነገር ግን የሚፈፀመው የማረሚያ ቤት ቅጣት ምክንያቱን ቤተሰቡና ታራሚው እንዲያውቁ ስለሚደረግ ማነጋገር ትችላላችሁ” የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

የወህኒ ቤቱ ጥበቃዎችና በዕለቱ ያሉ የኃላፊዎች ግን ስንቅ ይዘው ሊጠይቁ የሄዱትን የናትናኤልን ቤተሰቦች መገናኘት እንደማይችሉና የያዙትን ምግብ ይዘው እንዲመለሱ ከማዘዝ ውጭ የክልከላውን ምክንያት አልተናገሩም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ “ማረሚያ ቤቱ የራሱ አሰራር ስላለው አይደለም የፍትህ ሚኒስቴርና ኮማንደር አስቻለው ቀርቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ቢመጡ አያገባቸውም” ሲሉ በወቅቱ ስማቸውን ለማወቅ ያልተቻለ የዕለቱ የጥበቃ ኃለፊና ሁለት የጥበቃ አባላት ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጠኛ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

# UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

## በመላ ኢትዮጵያ እየተፈፀመ ያለው ግፍ ገዥው ፓርቲ ከአምባገነንነት በላይ መሻገሩን ያመለክታል!!!

### አምባገነኑ ገዥ ፓርቲ በአባላቶቻችን ላይ እየፈፀመ ያለውን ማሰር፣ መሰወር፣ ማሳደድና ማስፈራራት በአስቸኳይ እንዲያቆም እንጠይቃለን፤ ሥም እየተለጠፈባቸው በየማጎርያ ቤቱ የሚጣሉ የፖለቲካ እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ!

### ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ(አንድነት) የተሰጠ መግለጫ

የመድብለ ፓርቲ ስርዓትን ጨርሶ ለማጥፋትና ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ ለመሆን እንዲሁም ለረጅም ጊዜ በስልጣኑ ላይ ተደላድሎ ለመቆየት የሚያልመው አምባገነኑ የኢህአዴግ ስርአት በአባሎቻችንና አመራሮቻችን ላይ የሚያካሂደውን የማሰር፣ የማሳደድና የማስፈራራት ዘመቻ ፓርቲያችን ላይ ትኩረቱን አድርጎ አጠናክሮ ቀጥሏል።

ይህችን ትልቅ ሀገር በከፍተኛ ኃላፊነትና ሞራል ማስተዳደር እየተገባው ከዚህ ውጭ በመሆን ከኃላፊነትና ከሞራል ባፈነገጠና ጭካኔ በተሞላበት መልኩ አመራሮችና አባላት ላይ የተቀነባበረ ዘመቻ እያደረገ ይገኛል።
በአፍቅሮተ ስልጣን ተጠፍሮ ግራና ቀኝ ሳያይ ብቻውን ሽምጥ መጋለብ የሚፈልገው ኢህአዴግ የዜጎችን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥያቄዎችን በመመለስ ፈንታ ማፈንንና ማዳፈንን እንደ ልዩ ስትራቴጂ በማየት ይህንንም ለማስፈፀም የመንግስትነት ስልጣኑን ካለአግባብ በመጠቀም የፖለቲካ ምህዳሩን ከማዳፈንም ባሻገር አባሎቻችን ላይ እየፈፀመ ያለውን የማጥፋት ድርጊት አጥብቀን እንኮንናለን።

እንደዚህ አይነቱ እኩይ ድርጊት ለሀገርም ሆነ ለራሱ ለገዥው ፓርቲ ካለመበጀቱም በላይ ከፍተኛ ገንዘብ ተመድቦ ከትላልቅ ከተሞች እስከ ገጠር ድረስ እኛን የሚደግፉትንና አባሎቻችን የሆኑትን እግር በእግር እየተከታተሉ የሚያፍኑ ኃይሎችን በማዘጋጀት የሀገርን ሃብት የፓርቲ መጠቀሚያ እየሆነ እንደሆነ ልብ ለማለት ይገባል።
ጥቃቱ በመላው ኢትዮጵያ ባሉ የፓርቲያችን አባላትና ደጋፊዎች ላይ የሚፈፀም ሲሆን በተለይ በዚህ ወር ደግሞ በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል በከፋ መልኩ እየተፈፀመ ይገኛል። ሞራልና ስነ-ስርዓት በጎደለው ሁኔታ ይሰደባሉ፣ ይዛትባቸዋል፣ ይታሰራሉ፤ በመሆኑም አባሎቻችን ላይ እየፈፀመ ያለውን ድርጊት እዲያቆም እንጠይቃለን።

ባለፈው አንድ ሳምንት ብቻ እንኳን የሚከተሉት ጥቃቶች በፓርቲያችን አመራሮችና አባላት ላይ ተፈፅመዋል፡-

1. በምስራቅ ጎጃም፣ በባህርዳር ዙርያ፣ በሰሜን ጎንደር፣ ደባርቅና ታች አርማጭሆ አመራርና አባሎቻችን ካሉበት ቦታ እየታፈኑ ታስረዋል። ከነዚህም መካከል አቶ ጌቴ መቅጫ ከምስራቅ ጎጃም ጉምዶይን ወረዳ (የወረዳው ሰብሳቢ)፤ አቶ ነጋ አበጀ ከምእራብ ጎጃም ባህርዳር ዙርያ የዞኑ (ፀሐፊ)፣ አቶ ምቹ ተፈራ ከምስራቅ ጎጃም ጉምዶይን ወረዳ አባል፣ አቶ መስፍን ፀጋው ምስራቅ ጎጃም ጉምዶይን ወረዳ (አባል) እና አቶ ፀጋዬ እሸቴ ከሰሜን ጎንደር ደባርቅ ወረዳ እንዲሁም በደቡብ ክልል በደራሼ ከ06/07/2005 ዓ.ም ጀምሮ ታስረው በእስር ላይ የሚገኙ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) አባላት ስም ዝርዝር አቶ ቱኩ ከትክተው (አባል)፣ አቶ ኩባ ኪረኖ (አባል)፣ መምህር ካሱ ተፈራ (የወጣቶች ተጠሪ)፣ አቶ ዱባ ቱታ (አባል)፣ አቶ ጎኖኔ ኩልሴ (አባል) እና አቶ ወገኔ ኩልሴ (አባል) ናቸው።

ከላይ ስም ዝርዝራቸው የተጠቀሱ አባላት የፓርቲያችን አባላት ሲሆኑ ለልማትና ለምርጫ እንቅፋት ሆናችኋል በማለትና የተለያየ ስም እየተለጠፈባቸው የታሰሩ ናቸው። ከላይ ስማቸው ከተጠቀሱ አባላት ሌላ በመላ ኢትዮጵያ በርካታ ዜጎች የስርዓቱ የግፍ አገዛዝ ተጠቂዎች መሆናቸውን በተለያዩ መንገዶች ለማረጋገጥ ችለናል። ከጥቃቶችም መካከል ማሰሩ እንዳለ ሆኖ፡-

2. በደህንነት ሰዎች ዛቻና ማስፈራርያዎች በተደጋጋሚ ተፈፅሟል
3. አባሎቻችን የመሰብሰብ መብታቸው ተገፏል
4. የኢህአዴግ አባል ካልሆናችሁ የእርዳታ እህል ማግኘት አችሉም ተብለዋል
5. አባይ ወንዝ ላይ ለሚሰራው ግድብ በሚል ገቢያቸውን ያላገናዘበ መዋጮ እንዲያዋጡ ተጠይቀው ከአቅማችን በላይ ነው ስላሉ ብቻ ‹‹ፀረ- ልማት›› እየተባሉ የተለያዩ ጥቃቶች እንዲደርስባቸው ተደርጓል

ስለዚህ በፓርቲያችንና አባሎቻችን ላይ በቀነባበረ ሁኔታ የተከፈተው ዘመቻ እንዲቆም፤ የታሰሩ አባሎቻችንም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ እንጠይቃለን።

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ(አንድነት)

መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀመዛሙርት በፌደራል ፖሊስ ከግቢ እናስባርራችኋለን ተብለናል አሉ

### -የትምህርት ማቆም አድማውን በማጠናከር ጥያቄያቸውን የሚያብራራ ሰነድም አሰራጭተዋል

የኢትዮጵያ ኦርቶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ስላሴ መንፈሰሳዊ ኮሌጅ ደቀመዛሙርት ከመጋቢት 2 ቀን 2005 ዓ.ም. የጀመሩት የትምህርት ማቆም አድማ ተጠናክሮ እንደቀጠለና አሉብን ያሏቸውን ችግሮች የሚያብራራ ባለሰባት ገፅ ሰነድ ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨታቸውን ተማሪዎቹ የፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል፡፡ መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰራጨውና ለፍኖተ ነፃነት ዝግጅት ክፍል የደረሰው ሰነድ በመንፈሳዊ ኮሌጁ ያሉ መጠነ ሰፊ ችግሮች ነጥብ በነጥብ የሚያስረዳ ነው፡፡ በሰነዱ እንደተገለፀው ብፁዕ አቡነ ጢሞቲዎስ ወንበሩን ከያዙበት ጊዜ አንስቶ የመልካም አስተዳደር እጦት ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ የመኝታ እና የመፀዳጃ ቤቶች ጽዳት መጓደል፣እንዲሁም የምግብ ጥራት መጓደል አብዛኛውን ደቀመዝሙር ለበሽታ እንዳጋለጠው ተጠቅሷል፡፡ ትምህርት አሰጣጥን በተመለከተ የመምህራን ብቃት ማነስና የቤተ መጻህፍቱ ምቹ አለመሆኑን ከተማሪዎቹ ጥያቄዎች ውስጥ የሚጠቀስ ነው፡፡ ደቀመዛሙርቱ የኮሌጁ አካዳሚክ ዲን ተማሪዎችን፣መምህራንንና ሌሎች ሰራተኖች ላይ ድብደባና ዛቻ እንደሚፈፅሙ እንዲሁም “በአንድ ደቂቃ ግቢውን ለቃችሁ ውጡ ይህ ባይሆን ግን በፌደራል ፖሊስ በሃይል ከግቢው እናስለቅቃችኋለን” መባላቸውን አጋልጠዋል፡፡ ፍኖተ ነፃነት ከኮሌጁ ምላሽ ለማግኘት ያደረገችው ጥረት አልሳካም፡፡

# ባለሥልጣናት “ኢህአዴግን መምረጥ ግዴታ ነው” በማለት በማስፈራራት ላይ ናቸው

### -ኢህአዴግ ብቻውን እየተወዳደረም አልመረጥም ብሎ ሰግቷል

በተለያየ የመንግስት የሥራ ኃላፊነት ላይ ተቀምጠው ያሉ ካድሬዎችና ደህንነቶች ሠራተኞችንና ነዋሪዎችን በየቀበሌው እንዲሁም በተለያዩ አዳራሾች እየሰበሰቡ ኢህአዴግን መምረጥ ግዴታ እንደሆነ ከዛቻና ከማስፈሪያ ጋር መመሪያ እየሠጡ መሆናቸውን ምንጮቻችን ለፍኖተ ነፃነት አስታወቁ፡፡

የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና ደህንነቶች በተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ነዋሪዎች እንዲሰበሰቡ ካስደረጉ በኋላ ስብሰባው የተጠራበትን አጀንዳ በመተው “ኢህአዴግን መምረጥ ግዴታ ነው፤ ኢህአዴግን አለመምረጥ ፀረ ህዝብነት ነው፡፡” የሚሉና ሌሎች ማስፈራሪያዎችን እየሰጡ ነው ሲሉ ማንነታቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ መምህራንና የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር መጋቢት 11 ቀን 2005 ዓ/ም ነዋሪዎችን ስብሰባ ጠርቶ እንደነበር የሚናገሩት ምንጮቹ “ስብሰባ የተጠራነው ስለአካባቢያችን ልማትና መልካም አስተዳደር ላይ ለመወያየት ተብለን ነው፡፡ ስብሰባውን የመሩት የወረዳው ህዝብ ግንኙነት ኃላፊው አቶ አሰግድ (የወረዳው ኢህአዴግ ኃላፊ ናቸው፡፡) በስብሰባው ላይ ኢህአዴግን መምረጥ ግዴታ ነው፡፡ በሚል መንፈስ ዛቻና ማስፈራሪያ ሲናገሩ ውለዋል፡፡” ብለዋል፡፡ ምንጮቻችን አክለውም “ተሰብሳቢው በበኩሉ በየሠፈሩ ያሉትን ችግሮች እያነሳ ተናግሮአል፤ አንዳንዶቻችን እኛ ጥያቄአችን ምርጫ ሳይሆን የእለት ዳቦ ነው ብንልም ሰብሳቢው ተገቢ ያልሆነ መልስ ሰጥተውናል” በማለት ቅሬታቸውን ገልጸዋል፡፡

መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም የመዝናኛ ክበባት ሠራተኞች በክፍለ ከተማ ደረጃ ስብሰባ ተጠርተው ነበር፡፡ ከስብሰባው በኃላ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት “የተጠራነው አገልግሎት አሰጣጥ ጉዳይ ለመወያየት ተብሎ ነው፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግን መምረጥ ግዴታ እንደሆነ መመሪያ ተስቶናል፡፡ የፈለግነውን መምረጥ እንደምንችል ወይም ማንንም አለመምረጥ ህገ መንግስታዊ መብታችን መሆኑን ሊረዱልን አልቻሉም፡፡” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በዘንድሮ ምርጫ ነዋሪነታቸው ያልተረጋገጠና የቀበሌ መታወቂያ የሌላቸው ሰዎች ሁሉ በግዳጅ እንዲመዘገቡና ካርድ እንዲያወጡ ተደርጓል፡፡ የሚል ቅሬታዎች ሲናገሩ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ በመንግስት ደመወዝ እየተከፈላቸው ሙሉ ጊዜያቸውን የፓርቲውን ሥራ የሚሠሩና በመንግስት የሥራ ሰዓት ሠራተኞቻቸውን ለፓርቲው ሥራ የሚያውሉ የመንግስት ባለሥልጣናት በሙስና ወንጀል ሊጠየቁ ይገባል የሚሉ አስተያየቶችም እየተሰጡ ናቸው፡፡

በመጪው የአካባቢና የአዲስ አበባ መስተዳድር ምርጫ ብቻውን የሚወዳደረው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ላይ ላልመረጥ እችላለሁ በሚል ስጋት ነዋሪዎችንና ሰራተኞችን በስብበሳ ማዋከቡ ብዙዎችን እያስገረመ ነው፡፡

## መንግስት ህገወጥ የእስር. . . ከገፅ 1 የዞረ

ቢፈፀምም እስካሁን አንድም አባል ፍርድ ቤት አልቀረበም” ብለዋል፡፡ ይህ የመንግስት ዘመቻ የአንድነት አባላትን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸው ላይም ያነጣጠረ በመሆኑ የታፈኑት አባላት የት እንደሚገኙ ቤተሰቦቻቸው እንዲያውቁ እንደማይደረግም ታውቋል፡፡ ፍኖተ ነፃነት ለማጣራት እንደቻለችው የምስራቅ ጎጃም የአንድነት ጸሀፊ የሆኑት አቶ ነጋ አበጀ መጋቢት 6 ቀን 2005 ዓ.ም ጠዋት ወደ መስሪያ ቤት ሲሄዱ በመንግስት ሀይሎች ታፍነው ተወስደዋል፡፡ አቶ ነጋ አበጀ ታፍነው ከተወሰዱ በኋላ የታሰሩበትን ቦታ የሚነግራቸው የመንግስት አካል እንዳጡ የሚናገሩት ባለቤታቸው ወ/ሮ የኔነሽ ክንዴ መላ ቤተሰባቸው እንደተረበሸ ለፍኖተ ነፃነት ተናግረዋል፡፡

የከፋ የመንግስት ተፅኖ በአንድነት አባላት ላይ እየደረሰ ሲሆን በዞኑ የታች አርማጨሆ ወረዳ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ አንጋው ተገኘ መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ.ም ታስረዋል፡፡

ከደቡብ ክልል የተገኙ መረጃዎችም እንደሚያስረዱት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ ዜጎች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ እየታሠሩ ፍ/ቤትም ሳይቀርቡ በማን አለብኝነት እየታሰሩነው ፡፡ በተለይም የአንድነት ፓርቲ አባላት የዚሁ ጥቃት ሰለባ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከፓርቲው የክልል ጽ/ቤቶች ባገኘነው መረጃ መሠረት በደቡብ ክልላዊ መንግስት ጋሞጎፋ ዞን ደራሼ ወረዳ ውስጥ አቶ ተኩ ኮቲቶ ፣አቶ ኩባያ ኮራኖ፣ አቶ ወጫሬ አሌ ፣አቶ ካሱ ተፈራ፣ አቶ ዱባ ቱታ፣ አቶ ጎዳኔ ኩልሴ፣አቶ ወገኔ ኩልሴ የተባሉ የአንድነት አባላት ከመጋቢት 6 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ በእስር ላይ ይገኛሉ ፡፡

አንድነት “አባሎቼ የታሠሩት ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ነው፡፡ ከታሠሩበት ቀን ጀምሮ ቤተሰብ እንዳያገኛቸው ክልከላ ተደርጓል፡፡ ስንቅ አይቀርብላቸውም እስከ ዛሬ ድረስም ፍ/ቤት አልቀረቡም፡፡ ድርጊቱ የአገሪቱን ህገመንግስት የሚጥስ ነው፡፡” ሲል ድርጊቱን አውግዟል፡፡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት የአንድነት አባላትን በጅምላ ታስረውበታል ወደ ተባለው ደራሼ ከተማ ፓሊስ በተደጋጋሚ ስልክ ብንደውልም ስልኩን የሚያነሳ ባለመኖሩ

# አንድነት ፓርቲ ማተሚያ ማሽን በመግዛት የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ህትመት ለማስቀጠል የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀግብር ጀምሯል

እርስዎም :-

. ኩፖን በመግዛት

. የቃልኪዳን ሰነድ በመሙላት

. አቢሲኒያ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 47 ገቢ በማድረግ አጋርነትዎን ያረጋግጡ

ለተጨማሪ መረጃ

0933-89-17-66 እና

0933-89-17-67 ይደውሉ

udjparty@gmail.com

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ወደ ህትመት እንድትመለስ በመርዳት መረጃ የማግኘት መብትዎን ያስከብሩ!!

ፍኖተ ነፃነት

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ